# እረፍት ወይስ ሽሽት

በአለፉት ቀናት በውጭ የዜና ምንጭ በቀረበው ዘገባ የኢትዮጵያ ጠ/ሚኒስቴር አቶ ሃይለማርያም ደሳለኝ በኪራይ አይሮፕላን ከነቤተሰቡ ጀርመን እንደገባ ተገልጿል፣ሃተታው እንደሚጠቁመው አወጣጡ ለሕክምና ብሎም ለእረፍት እንደሆነ ሲሆን ሕክምናም የሚደረግለት በቁንጅና ቀዶ ጥገና በታወቀው የጀርመን ሆስፒታል መሆኑንና የሚያርፈውም ቀደም ሲል ለባለስልጣኖቹ መዝናኛ እንዲሆን በተዘረፈ የኢትዮጵያ ሕዝብ ገንዘብ በተገዛ የግል መኖሪያ ቤት እንደሆነ ዜናው ጠቁሟል።በማን ስም እንደሆነ ግን አልታወቀም።በተመሳሳይ መንገድ በየአገሩ ቤትና ንብረት እንደተገዛ የሚጠቁም መረጃ በሰፊው ይነገራል።

ለሕክምና መውጣታቱን መቃወም ባይቻልም አሁን አገሩ ኢትዮጵያ ባለችበት ቀውስ በተለይም ብዙ ሚሊየን ኢትዮጵያዊ የሚልሰው የሚቀምሰው አጥቶ በረሃብ አለንጋ ሲገረፍና ሲረግፍ፣የውጭ አገር ድርጅቶች የእርዳታ ጥሪ ሲያደርጉ እሱ በግል አይሮፕላን ተከራይቶ  ለሕክምና ለዚያውም ለቁንጅና ቀዶ ጥገና መውጣቱ እንኳንስ ከመሪ ከቀና ዜጋም የማይጠበቅ አድራጎት ነው።

ለሕክምና ወጣበት የተባለው በሽታ ድንገተኛና አደገኛ ሳይሆን ለብዙ ጊዜ ተሸክሞት የኖረውን የዓይን ጎባጣ ለማስተካከል ነው ተብሏል።እርግጥ ነው የዓይን ችግር እንዳለበት ማንኛውም ጤነኛ ዓይን ያለው አይቶ ይፈርዳል፣አይክደውም።የአቶ ሃይለማርያም ደሳለኝ በሽታ ግን ከውጭ የሚታየው የእይታ መዛባት ወይም የዓይን ቅድ መጣመም ብቻ ሳይሆን የውስጥም አመለካከት ችግር ጭምር ነው።እሱና የሚመራው መንግሥት አገሩንና ሕዝቡን የሚያይበት የጎሳ ዓይን አገሪቱን ገደል እየከተታት መሄዱን የሚክድ የለም።የኢትዮጵያ ሕዝብ አገርና ሕዝብ የሚጎዳ ፣በጎሳ መነጽር የሚይይበትን የፖለቲካ እይታ(አመለካከት) እንዲያስተካክል እንጂ የዓይንህ ቅድ አላማረኝምና በቀዶ ጥገና አስተካክልልኝ ብሎ አልጠየቀውም።የኢትዮጵያ ሕዝብ መሪዎቹን በሚሰሩት ሥራ እንጂ በመልክና በጎሳቸው የሚወድና የሚጠላ፣ የሚንቅና የሚያከብር አይደለም።

 እንደ አረመኔው መንግስቱ ሃይለማርያም አስቀድሞ ቤተሰቡን ማሶጣቱ ምናልባትም አሁን የሚመራው መንግሥት ባለበት ውጥረትና የእርስ በርስ ሽኩቻ ምክንያት በበሽታ ሰበብ ተገፍቶ ለአጭር ጊዜ ቆይታ ሳይሆን ለተራዘመ ስደት የወጣ ሊሆን እንደሚችል መጠርጠር ትክክል ሊሆን ይችላል።ያም ሆነ ይህ አቶ ሃይለማርያም በዚህ ቀውጢ ቀን ከቁንጅና ቀዶ ጥገና ጋር ለተያያዘ የዓይን ሕክምና መውጣቱ ምን ይህል እራሱን ወዳድና ለአገሩ ደንታቢስ እንደሆነ ያመለክታል። በጣም የሚገርመው ደግሞ የአገር ውስጥ የዜና ምንጮች ጉዳዩን በሚስጥር መያዛቸውና ለሕዝቡ አለመግለጻቸው ነው።ሕዝብና መሪ ሆድና ጀርባ በሆነበት አገር ሕዝብ የመሪውን የእለት እለት ተግባር አለመስማቱ የሚያስገርም ባይሆንም የዜና ተቋማት ምን ያህል ለሙያቸው ያላደሩና ሕዝባዊ አለመሆናቸውን የሚያሳይ መስተዋት ነው።የቀድሞውንም ጠ/ሚኒስቴር መታመምና መሞት የኢትዮጵያ ሕዝብ ዜናውን የሰማው በውጭ አገር ከሚተላለፈው  የዜና ተቋም ነው። የአሁኑንም ጠ/ሚኒስቴር በግል የኪራይ አይሮፕላን ወደ ጀርመን አገር መውጣትና  የሃብታሞች መኖሪያ በሆነው አነስተኛ ከተማ እንደገባ የሰማው በኢሳት በተባለው የዜና ስርጭት አማካይነት ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በሥልጣን የባለጉና መከራውን ያሳዩት መሪዎቹ በስበብ አስባቡ አገር ለቀው ሲወጡ ጓዛቸውን ጭኖ ሲሸኝ ይህ የመጀመሪያው አይደለም፤አስራሰባት ዓመት ሙሉ ስቃዩን ሲያሳዩት የነበሩት እንደ መንግስቱ ሃይለማርያምና ተከታዮቹ የመሳሰሉት ገዳዮች በውጭ አገር ቤትና ንብረት ገዝተው በሰላም እየተዝናኑ እንደሚኖሩት ሁሉ የዛሬዎቹም ወንጀለኛ መሪዎችና ባለሥልጣኖች  በዚያው መንገድ ለመንጎድ አያቅታቸውም።ያልተደራጀ ሕዝብ፣ጠያቂና የሚጠየቁበት ሕግ የሌለበት አገር ለዚህ የተመቸ ነው።የዛሬ ሃያ አምስት ዓመት ተኩል፣አገር ጥሎ ከመሸሹ በፊት መንግስቱ ሃ/ማርያም ለመሸሽ በዝግጅት ላይ መሆኑን ዘ ኦብዘርቨር(The observer) የተሰኘው የእንግሊዝ ጋዜጣ ገልጾ ነበር፤ያንንም መረጃ እኔና የቀድሞው አቶ የአሁኑ ፕሮፌሰር ማሞ ሙጨ ለንደን በተገናኘንበት ወቅት ተወያይተንበት ኢትዮጵያ ውስጥ ለምናውቃቸው ሁሉ ደብዳቤ በመጻፍ አሳውቀን ነበር።ጉዞው እንዲሰናከልና እንዳይሸሽ ግን የተደረገ ሙከራ አልነበረም።

ወንጀለኛው ከነቤተሰቡ በአሜሪካን መንግሥትና በአውሮፓውያን እንዲሁም በወያኔ የውስጥ ለውስጥ ስምምነትና ትብብር ጓዙን ጭኖ ወጣ።ተባባሪዎቹም ተከተሉት።የእኛ የኢትዮጵያውያን ድክመት ወንጀል ከመፈጸሙና ችግር ከመከሰቱ በፊት ከመከላከል ይልቅ ከተፈጸመና ከደረሰ በኋላ መንጨርጨራችን ነው።ጅብ ከሄደ ውሻ ጮኸ እንደሚባለው ተረት። መንግስቱ ሃይለማርያምን በጓዳ በር ሲያሶጡ በፊት በር የሚገባውን ወያኔን አዘጋጅተው ነው።አሁንም ወያኔ የሚቆጣጠረው ስርዓት ሊያገለግላቸው ካልቻለና ከተዳከመ በለመዱት መንገድ መሪዎቹ በሰላም የሚኖሩበትን ዘዴና የሚያገለግላቸውን ተተኪ ከማስቀመጥ አይመለሱም፤አሁንም ያዘጋጁት አልወጋ ወራሽ እንዳለ መጠርጠሩና መዘጋጀቱ ይመረጣል።ሃይለማርያም ደሳለኝ እንደ መንግስቱ ሃይለማርያም ተመሳሳይ እርምጃ ቢወስድ የሚያስገርም አይሆንም።ሌሎቹም መሪያቸው ሃይለማርያም በቀደደላቸው ጎዳና መቀጠላቸው የጊዜ ጉዳይ ነው አይቀርም ።ይህ ከመሆኑ በፊት ግን ከአለፈው ድክመት ተምሮ ወንጀል የፈጸሙ መውጫ ቀዳዳ እንዳያገኙ ሕዝቡ ተባብሮ ኬላውን መጠበቅና መዝጋት ይኖርበታል። በተጨማሪ መዘንጋት የሌለበት የውጭ ሃይሎች በኢትዮጵያ ላይ የመወሰን መብት እንደሌላቸው አውቀን እኛው በመረጥነው መሪና ስርዓት ለመተዳደር የሚያስችለንን የጋራ ዘዴ መፈለግ ይኖርብናል።ያ ካልሆነ ግን ዴሞክራሲ እየናፈቀን፣ ሌሎች በሚመርጡልን መሪና አስተዳደር ስንገዛ መኖር ይሆናል።

በውጭ አገር በተለይም በአውሮፓ የሚኖረው አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ሃይሉን አስተባብሮ ጠቅላይ ሚንስትሩ ባረፈበት ከተማ የተቃውሞ ሰልፍ በማዘጋጀት ለጀርመን መንግሥትና ሕዝብ ይህ ግለሰብ የሚመራው መንግሥት የሚፈጽመውን በደልና ከደሃ ሕዝብ ጉረሮ እየተነጠቀ የሚያካብተውን ቋሚ ንብረትና ሃብት ማጋለጥና ከተቻለም ለባለቤቱ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ተመላሽ እንዲሆን፣መጠየቅ ይኖርበታል። የአውሮፓ መንግሥታት በተለይም የጀርመን መንግሥት ሰብአዊ መብት ለጣሱ፣በወንጀል ለሚጠየቁና የሕዝብ ሃብት ለዘረፉ ወንጀለኛ መሪዎች አገራቸው ምሽግ እንዳይሆን ማስገንዘብ ተገቢ ነው።የውጭ አገር መንግሥታት በአገራቸው ውስጥ የኢትዮጵያ ባለሥልጣኖች በራሳቸውና በዘመዶቻቸው ስም ለሚገዙትና በባንክ ለሚያስቀምጡት ገንዘብ ምንጩ ምን እንደሆነ መከታተል ይኖርባቸዋል።አቶ ሃይለማርያም ደሳለኝ አረፈበት የተባለው ቤት ባደን ባደን በተባለው የሃብታሞች መኖሪያ ከተማ ሲሆን የቤቱ ዋጋ በሚሊየን ኤሮ የሚገመት ነው።ያንን አውጥቶ ለመግዛት ደግሞ የአቶ ሃይለማርያም ደሳለኝም ሆነ የሌላ ባለስልጣን ገቢ ላለፉት 25 ዓመት ቢሰላ ግማሹም አይሆንም፤ከየት የተገኘ ገንዘብ ነው?በተደጋጋሚ በተቃዋሚው ሲገለጽ የኖረው የባለስልጣኖቹ ዘረፋ እውነት ለመሆኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ነው።አቶ ሃይለማርያም ደሳለኝ ብቻ ሳይሆን በስልጣን ዙሪያ ያሉትና ተባባሪዎቻቸው በዘመድ አዝማዱ ስም ሃብት አካብተዋል።በውጭ አገር ባንክ ገንዘብ አስቀምጠዋል፣ቤትና ንብረት ሰብስበዋል።ይህን አድራጎት በሕግ የሚጠይቅ ብሔራዊ የሕግ ባለሙያዎች አካል መፈጠርና መከታተል ይኖርበታል።የሌሎች አገሮች የትግል ውጤትም ይህንን ያስተምረናል።

አሁን ጠቅላይ ሚኒስትሩ የፈጸመውን አላፊነት የጎደለው ተግባር በአውሮፓ የሚገኙ ለአገር አንድነት ፣ ለዲሞክራሲ ስርዓት መስፈንና ለሰብአዊ መብት መከበር የሚታገሉ የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶችና የሲቪክ ማህበራትና ግለሰቦች ሁሉ ተባብረው ማጋለጥ ይኖርባቸዋል።ሌላው ቢቀር በጀርመን፣በሆላንድና በቤልጅየም የሚኖሩት በቅርብ ቀናት ውስጥ ሕዝባዊ የተቃውሞ ሰልፍ ለማዘጋጀት የሚሳናቸው አይሆንም፤ስለሆነም ለጉዳዩ ትኩረት እንዲሰጡትና እንዲያዘጋጁ ጥሪ አደርጋለሁ።በተለይም በጀርመን አገር የሚኖሩት የተሰራጨውን ወሬ ማጣራትና በማስተባበሩ ቅድሚያ ሚና ሊኖራቸው ይገባል።ይጠበቅባቸዋልም።

አምባገነኖችን በየደረሱበት ማጋለጥ የአገር ወዳዱ ተግባር ነው!

ወንጀል ለማይሰራበት ሕጋዊ ስርዓት መስፈንና ዘርፈውና ገለው ለማይሸሹ ሃቀኛ የሕዝብ መሪዎች መፈጠር እንታገል!!

አንድነት በአንድነት!!!

አገሬ አዲስ